<u>ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም</u>

<u>ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ</u>
<u>የፌዴራል ዋና ኦዲተር</u>
<u>የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች</u>
<u>2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት</u>

<u>አጭር መግለጫ</u>

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፤ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ከንውን ሪፖርት እና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፣

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services III) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2006 በጀት ዓመት የተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች፣ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው 11 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 20 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም የ18 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ፣ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ 2 ጥራዞች (የልዩ ልዩ መ/ቤቶች የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርትና አጠቃላይ ዘገባ) ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ

የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2006 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሣብ

ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2006 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ የኦዲት ዕቅዳችን መሠረት ያደረገው እንደተለመደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትንና አዲሱን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 63/2 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤታችንም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች ሂሳባቸውን ዘግተው ሲያቀርቡ ኦዲቱን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ታህሣሥ 30 በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለኦዲት ተደራጊዎች ለመስጠት ግብ ጥሏል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው የኦዲት ካላንደርና ዘዴ ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዝጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ በተከታዩ ዓመት ታህሣሥ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 145 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 137 መ/ቤቶችን (ከ27 ቅ/ጽ/ቤቶች) በፌዴራል ዋና ኦዲተር የተቀሩትን ስምንቱን ደግሞ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ መታቀዱ ይታወሳል፡፡

በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 135 መ/ቤቶች (ሁለቱ ታጥፈው በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የተሰሩ ስለሆነ ዕቅዱ ከ137 ወደ 135 መ/ቤቶች ዝቅ ብሏል) መ/ቤቶች ውስጥ 133 (ከ26 ቅ/ጽ/ቤቶች) የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት አፈጻጸማችን 98.52% ሆኗል፡፡ አንድ መ/ቤት በሰው ኃይል እጥረት ተጀምሮ ያልተጠናቀቀ ሲሆን፣ የአንዱ ግን በመ/ቤታችን በኩል ተገቢው ጥረት ቢደረግም የወጣቶች ስፖርት አካዳሚ የ2006 በጀት ዓመት ሒሳቡን ሊዘጋ ባለመቻሉ ኦዲቱን ማከናወን አልተቻለም፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ133 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ300 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
	2005	2006	2005	2006	2005	2006
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	59	39	1	1	60	40
ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	49	63	280	299	328	362
አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው	7	11			7	11
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	15	20			15	20
ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ	2	1			2	1
ድምር	**132**	**134**	**281**	**300**	**413**	**434**

በፌዴራል መንግሥትመ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉን፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፤ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች ብር 79,241.55 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸው መቱ፤ ሚዛንና ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲዎች እና በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ7 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 490,647.11 በማነስ ልዩነት ታይቷል፡፡

12. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፤ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በቆጠራ ከተገኘው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ በማነስ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና የታዩት የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ

13. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ78

መ/ቤቶች ብር 2,025,166,722.68 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

14. ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 666,440,245.66፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 433,466,219.10፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 174,399,737.92፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144,266,244.06፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 102,154,467.22፣ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 77,514,902.99፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 64,943,966.34፣ የግብርና ሚ/ር ብር 64,408,202.66 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 39,294,784.18 ይገኙበታል፡፡

15. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቡ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ካልተሰበሰበ በቆየ ቁጥር የመሰበሰብና ወደ ሀብትነት የመለወጥ እድሉ ተዳክሞ ለብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ፣ እንዲያወራርዱ ወይም ከመዝገብ እንዲሠረዝ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

16. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሰረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

<u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

17. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥር ባሉ አስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,939,859.99 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የቀረ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

18. በአዋጁ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 118,073,560.67፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 9,960,926.18፣ የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 7,633,367.06 እና የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 7,507,248.72 እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር17,332,974.61 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

19. የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖሪት የመጫኛ፣ ማራገፍያና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

20. በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

21. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በሌሎች 12 መ/ቤቶች

በድምሩ ብር 1,039,493,043.58 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

22. ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 354,731,428.16 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ከጅንአድ እና አዲስ ፋና ያልተሰበሰበ)፣ የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 194,121,340.97፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 160,697,495.76፣ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 139,478,125.05፤ መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 44,990,059.02 እና የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,092,521.89 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

23. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ</u>

24. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች (ጎንደር፣ ዋቻሞ፣ መቐለ፣ ጅግጅጋ፣ አሶሳ እና ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች) የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 72,072,130.37 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም አንድ መ/ቤት /መቐለ ዩኒቨርሲቲ/ ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፈቃድ የገቢ ደረሰኝ በማሳተም ብር 12,879,067.34 ገቢ የሰበሰበ መሆኑ ተውቋል፡፡

25. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸውም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ፤ የመንግሥትን ገቢ ሰብስበው መዝገብ የማይይዙና የሚደብቁ መ/ቤቶች ላይ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

26. የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶችና በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 265,302,012.62 አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ /የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ የትራንስፖርት ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት እንዳለበት በተደነገገው መሠረት ከጅቡቲ ወደብ እስከ ቅ/ጽ/ቤቱ ደረቅ ወደብ ድረስ ለተጓጓዙበት የተከፈለውን ሂሳብ የሚያሳይ የትራንስፖርት ደረሰኝ (Inland freight invoice) ከዲክላራሲዮኑ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑና ተፈላጊ መረጃዎች በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ በመሆኑ፣ ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ቅጠል የገቢ ደረሰኝ የሚዘጋጅለት መሆኑና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፣ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

27. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ዋና ዋና

የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

28. በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

29. በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የጉምሩክ ስነ ስርአት አፈፃፀምና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 86/2005 ንዑስ ክፍል አራት (19) መሰረት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ላይ ተገቢውን ምርት ለውጪ ገበያ እያቀረቡ ለመሆኑና በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ቃሊት ቅ/ጽ/ቤት፣

- የቀረጥ መጠኑ ብር 28,252,497.56 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርዓት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 2,905,137.04 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርዓት ከቀረጥ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 700,946.29 የሆነ ጥሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ቢሆንም ያልተወራረደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከቀረጥ ነፃ በገባው ጥሬ እቃ ልክ ምርት ለውጪ ገበያ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፤

30. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 86 እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 አንቀጽ 26 በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ማጣራት በናሙና ከታዩት ውስጥ፡-

- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በታክስ ከፋይነት ተመዝግበው ነገር ግን ከተመዘገቡበት ጊዜ አንስቶ ወደ ታክስ ማዕከሉ መጥተው የማያሳውቁ 329 ግብር ከፋዮች፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ ባዶ / Nil / የሚያሳውቁ 88 ግብርከፋዮች መኖራቸው፡፡
- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብርና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳዉቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 6 ግብር ከፋዮች መኖራቸው፡፡
- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርንኦቨር ታክስ ተመዝግበው ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳውቁና ግብርም የማይከፍሉ

እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 27 ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በመንግስት ተቋም ከተቀጠሩ ሰራተኞች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት አሰሪው መስሪያ ቤት በመመሪያው መሠረት በወቅቱ እየሰበሰበ ገቢ እያደረጉ ለመሆኑ የሚከታተልበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌሎች መ/ቤቶች የሚታዩ የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

31. ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- በ4 መ/ቤቶች ብር 21,509,145.55 ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ከተቋራጮች ያልተሰበሰበ የመቀጫ ሂሳብ/የጉዳት ካሳ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የአለርት ማዕከል በ2005 በጀት ዓመት ከግል የህክምና አገልግሎት ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ የመንግሥት ድርሻ 15% ለሆስፒታሉ ገቢም፣ ፈሰስም ያላደረገ ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ የመንግሥት ድርሻ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበስቡ መሆናቸው፣
- የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በበጀት ዓመቱ ከፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 1,601,290.49 ላይ የሥራ ግብር ያልቀነስ እንዲሁም ለሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደው የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

32. በመሆኑም የመንግስት ገቢ የመንግስት የገቢ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ ገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

33. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውንና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

34. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 368,002,429.66 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

35. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ የቀረቡት ደረሰኞች የገዥውን ማንነት እንዲሁም ቀኑንና ነዳጁ የተሞላላቸውን፣ እጥበትና ግሪስ የተደረገለትን መኪና ሰሌዳ ቁጥሩን የማይገልጽ፣ የቀረቡት ተራ (አግባብነት የሌላቸው) ደረሰኞች ማለትም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

36. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

37. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ47 መ/ቤቶችና በሦስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 53,360,272.59 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

38. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈፀሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,309,358.20፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,183,248.07፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 6, 864,329.08፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,971,271.40፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,392,102.00 የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 3,286,245.49 እና የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,168,957.57 ሲሆኑ፤ ከምክንያቶቹም ዋና ዋናዎቹ ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች አበል፣ ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት /ከ1 እስከ 6 ወር/ የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

39. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

40. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ11 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 28,175,126.27 እና በ16 መ/ቤቶች ደግሞ ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 4,897,884.43 በጠቅላላው ብር 33,073,010.70 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

41. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ያለበቂ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ

በማድረግ ወይም ከተገባው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል፣ እንዲሁም ለትርፍ ሰአት፤ ለተለየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተተመነው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግና ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

42. በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትለው መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች</u>

43. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ63 መ/ቤቶችና ሦስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 957,510,040.14 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

44. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 743,797,845.69፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 95,008,585.46፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,144,748.02፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,641,407.32 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,791,692.29 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

45. ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸሙ እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

46. ከዚሁ በተጨማሪ በ4 መ/ቤቶች የብር 9,120,451.76 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎት ግዥ፤ የተፈጸሙ መሆኑ ተረጋግጧል።

47. የግዢ መመሪያንና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንቦችን ሳይከተሉ ግዢ መፈጸም ለምዝበራና ለጥራት መጓደል እንዲሁም ለግብር አለመሰብሰብና ስወራ ጭምር

የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የመንግሥት ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት</u>

48. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ12 መ/ቤቶችና በ1 ቅርንጫፍ በብር 6,802,769.45 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 32,128,296.51፣ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 41,189,738.68 እና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 2,734,486.29 በድምሩ ብር 76,052,521.48 ተገኝቷል፡፡

49. ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረትም ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል።

50. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

<u>በመስክ ላይ ለነበሩ ነገር ግን ግንባታ ላይ ላልዋሉ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) የተፈጸመ ክፍያ</u>፤

51. በፌዴራል የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ6 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 76,063,137.72 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ አላግባብ እንዲተካ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል በ2 መ/ቤቶች ለግንባታ ግብዓቶች በብድር ተሰጥቶ የነበረ ብር 16,727,198.50 ሳይቀናነስ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

52. በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች ብድር እንዲሰበሰብ እና የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

<u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

53. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በደንብና በመመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ለኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያና ለሌሎች ወጪዎች ብር 241,408,732.29 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡

54. ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 129,633,744.23፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 93,820,097.01፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,541,896.06 እና አማኑኤል ሆስፒታል ብር 2,876,348.12 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

55. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

56. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተሠርቶ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

57. በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ19 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 473,469,940.34 ተገኝቷል፡፡

58. ማስረጃ ሳይኖር በወጪ ከመዘገቡትና የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 273,845,378.34፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 110,930,205.38፣ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,443,824.20፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 11,599,720.78 እና ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 10,440,712.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

59. በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

<u>በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ</u>

60. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ወጪያቸውን በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 107,912,890.55 የወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገና በወጪ ሂሳብ ሪፖርትም ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

61. ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የመ/ቤቶቹን ትክክለኛ የፋይናንስ አፈጻጸምና ገፅታ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

62. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችንም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ብናሳስብም ሊታረም ባለመቻሉ በም/ቤቱ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

63. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ45 መ/ቤቶችና በሶስት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 973,746,519.63 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 460,160,937.67፣ ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 330,805,868.99፤ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 43,306,907.03፤ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 71,434,198.75 እና ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,535,123.38 ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

64. ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አስገዳጅ ሕጎች መሰረት ገቢ ሰብስበው የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ በ15 መ/ቤቶች ብር 41,374,483.14 መኖሩ ተረጋግጧል። ይህም የተከፋይ ሂሳብ ከተለያዩ ቅጣት፣ ከሰነድና መድኃኒት ሽያጭና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ሂሳብ ይጨምራል፡፡

65. በመሆኑም የተመከከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ሊከፈል ይገባል።

በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች

66. በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ተገቢው ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 164,658,370.51 መኖሩ፣
- በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ በ5 መ/ቤቶች ብር 42,641,122.73 መገኘቱ፣

- አላግባብ በዕዳ ወይም ተከፋይ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 19,683,605.46 መገኘቱ፣
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ በ2 መ/ቤቶች ብር 2,534,141.80 መታየቱ፣
- የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 65,766,617.35 መኖሩና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ከተቀጽላ ሌጀር አዘገጃጀትና አያያዝ ችግሮች እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል።

67. በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

<u>የበጀት አጠቃቀም</u>

<u>ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ</u>

68. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ37 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት የበጀት ዝውውር በማድረግ ሳይፈቀድ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ፣ ከመደበኛ በጀት ብር 232,148,072.37 እና ከፒታል በጀት ብር 3,163,827.82 በድምሩ ብር 235,311,900.19 ተገኝቷል፡፡

69. ከተደለደለው ከተደለደለደው በጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካከል፣ ውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ብር 37,915,592.09 ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 27,926,536.04 አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 31,741,412.73፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,712,013.47፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,422,282.30፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 14,825,649.05 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 14,250,809.51 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

70. ከዚህ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶች ብር 38,473,539.74 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቅድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ አድርገው የተጠቀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

71. በመሆኑም መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

<u>**ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት**</u>

72. የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ99 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 1,027,319,514.59 እና ካፒታል በጀት ብር 1,549,338,191.03 በድምሩ ብር 2,576,657,705.62 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ሁለት መ/ቤቶች ከተፈቀደላቸው ከውስጥ ገቢ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ ብር 24,693,679.88 ተገኘቷል ፣

73. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፣ ትምህርት ሚ/ር ብር 588,887,158.78፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 396,086,596.34፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 204,362,089.53፣ የኢፌዲሪ ስፖርት ኮሚሽን ብር 195,186,880.58፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 94,374,733.95፣ የከተማ ልማት፤ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 97,582,653.71 እና ደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ ብር 88,024,688.01 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

74. በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀዱትን ስራዎች ማይከናወኑ ሊቀሩ ስለሚችሉና የመ/ቤቱን ዓላማ ከማሳካት አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል በመሆኑ ለወደፊቱ መ/ቤቶች የሚያቀርቡት የበጀት ጥያቄ በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የንብረት አስተዳደር

75. መንግሥት ለቋሚና አለቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር በዚህም ዓመት አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	22 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱ ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	11 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	30 መ/ቤቶች
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረት የተገኙባቸው	31 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	43 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	12 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

76. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራ፤ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

77. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ20 መ/ቤቶች	192 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ23 መ/ቤቶች	247 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ1 መ/ቤት	4 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡

78. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው አሳስበናል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ

79. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍነው የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

80. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ PBS III ስምምነትን ተከትሎ በተሻሻለው የኦዲት ስምምነት መሠረት ተከታታይ ኦዲቱ በሀጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ፤ የኦዲት ውጤቱ የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን በተወሰነው መሰረት ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

81. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ300 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ300 (100%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ ለመፈጸም ተችሏል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ

ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ

82. በገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች ደግሞ የሚከተሉU ናቸው፡፡

83. የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመልሶ ማበደር ለስኳር ፋብሪካዎች ከሰጠው ብድር ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም ድረስ መሰብሰብ የነበረበት ብድር መሰበሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወለድና ቅጣትን ጨምሮ ብር 418,803,484.57 ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል ፡፡

84. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/ሀ መሰረት የበጀት ዓመቱ ሂሳብ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአጠቃላይና ተቀፅላ ሌጀሮች መነሻ ሚዛን ከ2005 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሚዛን በትክክል መተላለፉንና ሂሳቡም ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2005 በጀት ዓመት የዞረ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ ለ2006 በጀት ዓመት መነሻ ምዝገባ በሂሳብ መደብ 4210 የተመለከተው ብር 32,653,472.28 ከመቼ ጀምሮ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንደተመዘገበና ሂሳቡም የምን እንደሆነ የተቀፅላ ሌጀር ተለይቶ ባለመመዝገቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቸለ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ከ2005 በጀት ዓመት የዞረ ተብሎ ለ2006 በጀት ዓመት መነሻ ተደርጎ በሂሳብ መደብ 5052 ብር 13,274,435.33 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5054 ብር 8,251,376.10 በድምሩ ብር 21,525,811.43 የተከፋይ ሂሳብ ከመቼ ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ እንደተመዘገበና ሂሳቡም የምን ሂሳብ እንደሆነ በተቀፅላ ሌጀር ተለይቶ ባለመመዝገቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች በተመለከተ

85. የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱ ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ መ/ቤታችን ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ በማድረግ በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ

ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታታቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

86. በዚሁ መሠረት ከጥር 2006 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት ዓመት የዞሩ 6፤ ከጥር 2006 በኋላ ተጀምረው እስከ ታህሣስ 30 የሚጠናቀቁ 16፣ እንደዚሁም ኦዲታቸው ተጀምሮ ወደ ተከታይ ዓመት የሚሻገሩ 6 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

87. በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲት አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት ከዞሩት 6 ኦዲቶች ውስጥ፣ የ1 ኦዲት በሰው ኃይል እጥረት እና 1 ሌላ ኦዲት ደግሞ ከስልጣን ክልል ወሰን ውጭ በመሆኑ ምክንያት እንዲቋረጡ ተደርጎ 20 ኦዲቶች ለማከናወን ተስተካክለው ከታቀደው ውስጥ 18 ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው ተልኳል፡፡ ሁለት ኦዲቶች ደግሞ ስራቸው በዝርዝር ኦዲትና ሪፖርት ዝግጅት ደረጃ ወደ ቀጣይ ዓመት የተላለፉ ሲሆን፣ ተጀምረው እንደሚተላለፉ ከታቀዱት ኦዲቶች አንዱ ኦዲት ብቻ ተጀምሮ ተሻግሯል::

88. ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት 18 ኦዲቶች (90%) ሲሆን፣ የኦዲት ስራቸው ተጀምረው የዞሩት 3 ኦዲቶች በመሆኑ፣ ካጋጠመን ከፍተኛ የሰው ኃይል እጥረት አንጻር ሲታይ ዕቅድ ክንውኑ አጥጋቢ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይሁንና ኦዲተሮቻችን ባደረጉት ከፍተኛ ጥረትና ግፍት ከታቀደው ውስጥ ከ90% በላይ መፈጸም ቢቻልም የኦዲቶቹ የጥራት ጉዳይ አሁንም ሰፊ ሥራና ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ተገቢውን ትኩረትና ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል፡፡

89. የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 18 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች ሪፖርቶቹ ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶች በአጭሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና አቅም ለመገንባት የሚሰጠውን ድጋፍ እና ክትትል በተመለከተ

90. ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው 52 ኢንዱስትሪዎች ለሁሉም የካምፓኒ ፕሮፋይል ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤ በኢንስቲትዩቱ የተያዘው

የኢንዱስትሪዎችን ዝርዝር መረጃው ያልተሟላ መሆኑ ማለትም (የድርጅቱን አላማ፣ የካፒታል መጠን፣ ወደ ሥራ የገባበት ዘመን፣ የተጠቀማቸው ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አይነት፣ ለአገር የፈጠረው ፋይዳ ማለትም በስራ እድል፣ በአመት የማምረት አቅም፣ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ፣ የሚጠቀመው ግብአትና መጠን ወዘተ) መሆኑ፤ የዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ተመን መግለጫ የተዘጋጀ ቢሆንም ማስረጃውን ለሚጠይቁ ብቻ የሚሰጥ እንጂ መረጃውን የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ በመጠቀም ለምሳሌ በመረጃ ድረ ገፅ (web-site) ያልተቀመጠ መሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ ስለሚሰጣቸው ድጋፎች ለህብረተሰቡ በሚገባ ያላስተዋወቀ መሆኑ፤

91. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ ሆኖም ግን ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ የሚረዳቸው ቢሆንም ድጋፉን ስለማግኘታቸው ክትትል የማያደርግ ከመሆኑንም በላይ ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የማይከታተል መሆኑ፤

92. ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የግብይት ስትራቴጂ ለመንደፍ እና ተጓዳኝ ድጋፍ ለማድረግ ከ2004-2007 በስትራቴጅክ እቅድ ቢይዝም በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ያልገለፀና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

<u>ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ብቃት ያለው ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ</u>

93. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ኃላፊነት እና ከገቢና ወጪ (import & export) ንግድ አንፃር ለህገ-ወጥ

የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ሊለዩ የሚገባ ቢሆንም የህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ለይተው ያላስቀመጡ መሆኑንና የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከልም እነዚህ አካላት ግዴታቸውን አውቀው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ አላማድረጉ፤

94. በብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንጽ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሄራዊ ባንክ የተለየ ፍቃድ ካላገኘ በስተቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሰማራት እንደማይፈቀድ የተደነገገ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች (በአዲስ አበባ ስታዲዮም አካባቢ፣ በብሔራዊ ባንክ ዋና መ/ቤት አካባቢ፣ በጋንዲ ሆስፒታል አካባቢ ወዘተ..) ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ በግልፅ እንደሚካሄድ በኦዲቱ ወቅት ከብሔራዊ ባንክ ከተገኘው መረጃ እና በሥፍራው በአካል በመገኘት በማየት /Physical Observation/ መታወቁ፤

95. የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት /ድርጅቶች/ የደንበኞቻቸውን ማንነት /customers identification and due diligence/ ጠንቅቀው ለማወቅ የሚረዳቸው አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ሁለት የመንግስት ባንኮች እና አራት የግል ባንኮች በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ ባለመኖሩ አንዳንድ ደንበኞች የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ሲመጡ ከአንድ መታወቂያ በላይ የሚጠቀሙ ስለሆነ የደንበኞችን ማንነት ሙሉ ለሙሉ እንዳያውቁ እንቅፋት እንደሆነባቸውና ሥርዓቱን ለመዘርጋትም መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡

96. በተሻሻለው የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ3. ላይ የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ በማቅረብ (over or under

invoicing of imported or exported goods) በሚሳተፉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ከሌሎች ቅጣቶች በተጨማሪ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ንብረት ሶስት እጥፍ እንዲከፍሉ የተቀመጠ ቢሆንም በብሄራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ በሚያቀርቡት ላይ በአዋጁ መሰረት እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነ እንዲሁም ለፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤

97. የንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር እና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ እና ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ እንዲሁም በውጭ አገር ሥራ በማስቀጠር አማካኝነት የሚገኝ የውጭ ምንዛሪም ሆነ ብር በሕገወጥ መልክ ያዘዋውራሉ ብለው የሚጠረጥሩትን ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚገባ ቢሆንም በዚህ መልኩ የሚደረግ ህገ ወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውርን በተመለከተ ለማዕከሉ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

<u>የግብርና ኤክስቴንሽን በተለይ የሰብል ኤክስቴንሽን አፈፃፀምን በተመለከተ፣</u>

98. ለአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ የኢንደስትሪ ግብዓት የሚሆን የሰብል ምርት አርሶ አደሩ እንዲያመርትና ከኢንደስትሪ ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊሰጥና ስለአፈጻጸሙም በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም በሀገሪቱ ከፍተኛ ምርት ከሚገኝባቸው ሰብሎች አንዱ ስንዴ መሆኑና ይህንንም ጥሬ ዕቃ በመጠቀም በርካታ የዱቄት ፋብሪካዎች ቢመሰረቱም በተለይ ዱረም ስንዴ በበቂ መጠንና ጥራት በሀገር ውስጥ ባለመመረቱ ስንዴ ከውጪ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑ

99. እያንዳንዱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠርያና መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ እንዲኖረውና ወቅታዊ የሆነ የአየር ሁኔታ ዘገባና ትንበያ መረጃ እንዲያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ ክልሎች በሚገኙ 16 የአርሶ

አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ያሉ የስራ ኃላፊዎችና አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እንዲሁም በአካል በመገኘት ለማየት እንደተቻለው አስራ ሁለቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ የሌላቸው መሆኑን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያ በተሟላ መልኩ እንደማይሰጡ እና የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ሲገልፁ፣ በቀሪዎቹ በአማራ ክልል በሚገኙ አራት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ሬንጌጅ ብቻ እንዳለና ይህንን መሠረት በማድረግ የተሟላ ባይሆንም የዝናብ ሁኔታ መረጃ ለመስጠት እንደሚሞክሩ መገለጹ፤

100. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች ትምህርት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ በማሰባሰብ በቋሚነት የሚታዩበት ቋሚ ኢግዚቢሽኖችን በተመለከተ በ2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መመሪያ ላይ የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን፣ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን፣ የተለያዩ የአረም አይነቶችን፣ የሰብል በሽታዎችን፣ ሰብል አጥቂ ነፍሳትና ተባይ ናሙናዎችን፣ የግብርና ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለኤግዚቢሽኑ በተዘጋጀ ቦታ እንዲያስተዋውቁ የሚል ቢሆንም በናሙና በታዩት ክልሎች ባሉ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ይህንን ማየት አለመቻሉ፤

101. በግብርና ኤክስቴንሽን በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያ እና በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎች ላይ በእኩል ሁኔታ ሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተጠቃሚነታቸውንም ለማረጋገጥ እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና የባህልንም ተፅዕኖ መቀነስ ባለመቻሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል ኤክስቴንሽን ላይ የመሳተፍ ችግር እንዳለ፣ በዕቅድ ደረጃ ሴቶች 30 በመቶ ወጣቶች 10 በመቶ ተጠቃሚ ይሁኑ የሚል ቢሆንም ለሴቶች ስልጠና ተዘጋጅቶ ለመስጠት ሲሞከር ወደ ስልጠና የሚወጡበት ሁኔታ ባለመኖሩ ዕቅዱን ተፈፃሚ ለማድረግ እንዳልተቻለ፣ ወጣቶችን በተመለከተ በተለይ በ2006 ዓ.ም ተደራጅተው በተለያየ የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ስራ እየተሰራ ቢሆንም የመሬት ፍላጎታቸውን ማሟላት ባይቻልም ወጣቶችን

ተሳታፊ ለማድረግ መሬት በኮንትራት ተከራይተው እንዲሰሩ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ መሆኑ፤

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቱዩትን በተመለከተ

102. ተማሪዎች ስልጠና በሚወስዱበት ጊዜም ሆነ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ሊሟሉ ሲገባ አብዛኞቹ መለማመጃ ማሽኖች ተቋሙ ሲመሰረት /ከ40 ዓመታት በፊት/ ጀምሮ የነበሩ መሆናቸውና በወቅቱ የነበረው የተማሪዎች ቁጥር 70 እና 90 ሲሆን በ2005 ዓ.ም ከተቀበለው የተማሪ ብዛት 945 ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በጣም ሰፊ መሆኑን የተማሪው ቁጥር ሲጨምር የማሽኖች ቁጥር ያልጨመረ ከመሆኑም በላይ አሁን ያሉት ማሽኖችም በከፊል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው ፤

103. ማዕከሉ ከነሐሴ 08/1989 ዓ.ም ጀምሮ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት በራስ ሆቴሎች አስተዳደር ድርጅት ስር የነበረው የገነት ሆቴል ድርጅትን ለሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛነት እንዲያውል የተወሰነ ሲሆን በዚሁ መሠረት ማዕከሉ በገነት ሆቴል ታችኛው ግቢ ባለ ሶስት(3) ኮከብ ሞዴል ሆቴል ለመገንባትና ለመቆጣጠር ባክቴክ በተባለ አማካሪ መሐንዲስ ድርጅት የሞዴል ሆቴል ዲዛይን በመዋዋል ጥናት ተዘጋጅቶ የቀረበ ቢሆንም የግንባታ ስራዎች ሳይሰሩ አራት ዓመት በማስቆጠሩ ከባክቴክ አማካሪ ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ሲሆን የሞዴል ሆቴል ግንባታ ስራ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፤

104. ሰልጣኞች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠና እንዲያገኙ ለማስቻል በ1998 ዓ.ም ጌዲዮን ደመቀ የተባለ አማካሪ መሐንዲስ በገነት ሆቴል የሚገኙ 104 የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማሰልጠኛና የተግባር መለማመጃ ክፍሎች ለመቀየር የዲዛይን ሥራን ጨረታ በማሸነፍ የዲዛይን ጥናት በማካሄድ ዲዛይን ሰርቶ ያቀረበ ሲሆን በዲዛይኑ ላይ በክለሳ ወቅት አስፈላጊ የሆነ የብረት አይነት በአግባቡ አለመጠቀሱ በሬንቦ አርክቴክቸር ተቆጣጣሪ መሐንዲስ በመገለፁና በዚሁ መሠረት ጌዲዮን ደመቀ ተቋራጭ አሟልቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ብር 86,250 ከተከፈለ በኋላ ዲዛይኑም ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ መሆኑ፤

105. በመቀጠልም በ2000 ዓ.ም. የግንባታ ስራውን ለመቆጣጠር በጨረታ ያሸነፈው ሬይንቦ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ካሸነፈበት ዋጋ ከ25 በመቶ ባልበለጠ ዋጋ ስትራክቸራል ዲዛይኑን ያለጨረታ እንዲሰራ መደረጉ፣ ሬይንቦም የዲዛይን ጥናቱን በማዘጋጀት ያቀረበ ሲሆን ትክክለኛነቱ ሳይገመገም(ሳይጣራ) ለዚሁ ሥራ ብር 237,950 የተከፈለው መሆኑን እንደገና በ2001 ዓ.ም ሬንቦ አርክቴክቸር ለሁለተኛ ጊዜ ባዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ከሳሙኤል ሣህለማርያም ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ጋር የግንባታ ሥራውን ተዋውለው ተቋራጩ የዕድሳት ሥራውን ከጀመረና ብር 4,177,119 ከተከፈለው በኃላ ዲዛይኑ ችግር ያለበት መሆኑን በመግለጹ ከሰኔ 22/2003 ዓ.ም.ጀምሮ ውሉ መቋረጡ፣ እንደዚሁም በ2002 ዓ.ም ለዚሁ የግንባታ ዕድሳት ስራ ኤም ኤች ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ለሶስተኛ ጊዜ የዲዛይን ሥራውን እንዲያከናውን የተደረገና ብር 267,882 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ለሶስተኛ ጊዜ ባቀረበው ዲዛይን መሰረት ለግንባታ ሥራው የተጠየቀው ዋጋ ከብር 10,318,719 ወደ 23,503,293 በ127.8% ከፍ በማለቱ እና ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ ከሳሙኤል ሣህለ ማርያም የስራ ተቋራጭ ጋር የነበረው ውል ከሰኔ 22/2003 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑ፣

106. በአጠቃላይ የኦዲት ቡድኑ ተጀምሮ የተቋረጠውን የግንባታ ስራውን በመስክ በተመለከተበት ወቅት በሮችና መስኮቶች የሌሉት፣ ኮርኒሶች የተነቃቀሉ፣ የመታጠቢያ ቤት ዕቃዎች በሜዳ ላይ የተጣሉ መሆናቸው፣ በግቢው ውስጥ እና በግንባታው ቦታ ሳርና የተለያዩ እፅዋት በቅለውበት መታየታቸው በአጠቃላይ ለዕድሳት ስራው ከተለያዩ ወጪዎች ጋር ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት መሆኑን እና ውጤታማ አለመሆኑን በተደረገ የመስክ ምልከታና ከክፍያ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋፊና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረገው ሽግግር አፈጻጸም በተመለከተ

107. አገር አቀፍ የራዲዮና የቴሌቪዥን የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክት በተቀመጠለት ጊዜ በዕቅዱ መሰረት ተጠናቆ ሥራ ሊጀምር ሲገባ በ2001 ዓ.ም የተጀመረው አገር አቀፍ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሻሻያ እና ማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የመሣሪያ ግዥውና የህንፃ ግንባታው ተጠናቆ

ማሠራጫ መሣሪያዎቹን በመትከል ሥርጭት ይጀምራል ተብሎ በፀደቀ የጥናት ፕሮፖዛል ላይ ቢገለፅም የህንፃ ግንባታው በሦስት ዓመት፣ የዲጂታል ስርጭት ሽግግሩ ደግሞ በሁለት ዓመት የዘገየ ሲሆን የአንድ (ደርባ) ማሰራጫ ጣቢያ የትራንስሚሽንና የታወር ግንባታ ኦዲቱ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣

108. የዲጂታል መቀበያ መሳሪያዎች በዋነኝነት ሴት-ቶፕ ቦክስ፣ ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV) እና UHF አንቴና ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን እና የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች ለዲጂታል ሥርጭት ወደ DVB- T2 (Digital video Broadcasting Terrestrial 2nd generation) የመቀየር ሥራ፣ የSet Top Box (የዲጂታል ቴሌቪዥን ትራንስሚሽንን ለማየት ከቴሌቪዥን ጋር የሚገጠመው ዲኮደር)፣ የትራንስሚተር አፕግሬድ (Transmitter Up Grading) እና የሄድ ኢንድ (Head End) ሥራ በተመለከተ በጥናቱ ወይም በዕቅዱ መሠረት በ2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲገባቸው ስራው ያልተጀመረ መሆኑ::

109. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው ሽግግር የተዘጋጀው ፕሮጄክት ስራን ፕሮጀክቱን የሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ በኮንትራት ውሉ በተቀመጠለት የገንዘብ መጠን መሰረት ማከናወን እና ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚደረገው የሽግግር ስራ በሁለቱም ዙር (1st phase እና 2nd phase) የትራንስሚሽን ቴክኖሎጂ ገጠማው፣ ዲጂታል ስትዲዮና ተጓዳኝ ስራዎች በፕሮጄክቱ ጥናቱ ሠነድ የተሟላ ባለመሆኑና ተገቢውን ሁሉ ወጪ ባለመካተቱ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ብር 642,096,007 (ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ዘጠና ስድት ሺህ ሠባት ብር) 58% ወጪ የተደረገ መሆኑ፡፡

110. ለማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክትን የግንባታ እና የቁጥጥር ሥራ ላይ የሚሳተፉትን ተቋራጮች ሆነ አማካሪዎች የአገልግሎት ግዢው ሲከናወን በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ሊከናወንና ከአሸነፊው ድርጅትም ጋር የኮንትራት ውል ሊገባና ሥራውም በውሉ መሠረት ተፈጻሚ ሊደረግ ሲገባ ኮርፖሬሽኑ የቴክኖሎጂ ገጠማውን ሥራ ለማከናወን በብር 686,426,736.42 ከአንድ አቅራቢ ቻይና ፖሊ ቴክኖሎጂስ (china poly technologies inc.) ከተባለ ድርጅት

ጋር በሁለት ደረጃ (ፌዝ) ተከፍሎ ዋጋውም በድርድር እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል፡፡ ግገርው በድርድር እንዲፈጸም የተፈቀደ ቢሆንም በግገር አዋጅ አንቀጽ 52 መሠረት ለድርድር የሚሆኑ ትኩረተ ነጥቦች ፀድቀው ለተደራደሪው ቡድን አለመሰጠቱ፤

111. የአርካይቭ ስርዓት ዲጂታላይዝ ማድረግ ስራ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በጀት ዓመት በየዓመቱ ይተገበራል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም የትግበራው ስራ ግን እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ያልተጀመረ መሆኑ፤

112. በማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ታሳቢ ተደርጎ በሁሉም ክልሎች የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች እንዲገነቡና ችግሩን እንዲቀረፍ የሚል ቢሆንም በ11 ማሰራጫ ጣቢያዎች (ጂንካ፣ ሀርገሌ፣ ፊቅ፣ ማጂ፣ ዲቾቶ፣ ጮቄ ተራራ፣ አዲረመፅ፣ ዋርደር፣ ቀብሪ ደሃር፣ አዳባ ዲንሾ፣ ጉባ እና ጐዴ የማሠራጫ ጣቢያዎች) በየሳምንቱ ከሰኞ እስከ አርብ ለ5፡00 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ለ10፡00 ሰዓት ብቻ ስርጭት እያከናወኑ መሆናቸው፡

የሶስተኛ ወገን መድን ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ

113. የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በሚከፍሉት የአረቦን ተመን ላይ ተጨማሪ አስር በመቶ (10%) ተሰልቶ እንዲከፍሉ በማድረግ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሊሰበስቡ፤ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለሚያስገቡት የመድን ፈንድ ሂሳብ ኤጀንሲው የሶስተኛ ወገን መድን ፈንድ የሂሳብ መዝገብ ሊዘጋጅና የፈንዱም ሂሳብ በየዓመቱ ኦዲት ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም ኤጀንሲው ስራ ከጀመረበት ከ2004-2006 ዓ.ም ድረስ ለተሰበሰበው የመድን ፈንድ ገንዘብ የሂሳብ መዝገብ ያልተዘጋጀለትና ፈንዱ መሰብሰብ ከተጀመረ ጀምሮም ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ እንደዚሁም የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ባልተገባባቸውና ገጭተው በሚያመልጡ ተሽከርካሪዎች ለደረሰ የአካልና የሞት አደጋ ጉዳት የካሣ ክፍያ መክፈል ከጀመረበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የከፈለውን የካሣ ክፍያ ገጭተው የሚሰወሩ አሽከርካሪዎች በፖሊስ ክትትል በቁጥጥር ስር ባለመዋላቸው ለተጐጂዎች የተከፈለው የካሣ ክፍያ /ብር 1,186,594/ በሙሉ አደጋ ካደረሱት አካላት ያልተመለሰ መሆኑን፣

114. የተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ማንኛውም ህብረተሰብ በማንኛውም የጤና ተቋማት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡ ለዚህም ኤጀንሲው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ በ2003 ዓ.ም አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የጤና ቢሮዎች ያሰራጨ ሲሆን በ2006 ዓ.ም በድጋሚ መመሪያው የታተመና የጤና ቢሮዎች መመሪያውን ለመንግስት የጤና ተቋማት ያስተላለፉ ቢሆንም ለግል የጤና ተቋማት ያላስተላለፉና በመመሪያው መሰረት የጤና ተቋማት ስራ ያልጀመሩ መሆናቸው፣

115. የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ማንኛውም ጤና ተቋም ለመጣ አካል እስከ ብር 2,000 ድረስ በጤና ተቋማት አገልግሎት ከተሰጠ በኋላ የጤና ተቋማቱ ሂሳቡን ከየክልላቸው ጤና ቢሮ እንዲጠይቁ ለማድረግ ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ የጤና ቢሮዎች የየራሳቸውን አካውንት ለመክፈት በሂደት ላይ ስለሆኑ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ስራ ያልጀመሩ መሆናቸው፣

<u>በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም አገልግሎት ብቃት ማረጋገጥን በተመለከተ</u>

116. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ፖሊሲ በማዘጋጀት ለክልሎችና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ያሰራጨ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የአዲስ አበባ መስተዳድር ባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች በክልልም ሆነ በዞን እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ያሉ ቢሮዎች ላይ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አለመሆኑ፤

117. ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ሊወጣላቸው እና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም የባሕል ምግብ ቤቶች የአገሪቱን ባህልና ልማድ በበጎ ጎኑ የሚያንጸባርቁ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ

በክልሉ የባሕል ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች ምን መስፈርት ሟሟላት እንደሚገባቸው መስፈርት እንዳልወጣላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

118. በኮከብ ደረጃ የሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የሚገነቡበት ስፍራ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ ሊካተት ይገባዋል፡፡ በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ንድፍ ስራ ከመጽደቁ በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪስት ቢሮዎች በኩል ለሆቴል አገልግሎት አመቺ መሆኑን የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ሲገባው አለመደረጉ፤

119. በሆቴል ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሃብቶች በህግ የተቀመጠው የመገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ በማስገባት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ባለሀብቶች የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ሲጠይቁት የተጠየቀው ዕቃ ከሆቴል ስራ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ዝርዝሩን በማየትና በማረጋገጥ ሊፈቅድላቸው ይገባል፡፡ ወደ አገር ውስጥ በማበረታቻው ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ የሆቴል የቁሳቁስ እቃዎች፣ የፊኒሽንግ ማቴሪያል እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ሲገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡

120. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በአማራ፤ በኦሮሚያ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተላከ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣ ሎጆች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ የተጠየቀው ዕቃ ከስራው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የተጠየቀው ዕቃ ብዛትና ዓይነት የማያዩና ዕቃዎቹና መሣሪያዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ተዘርዝረው የሚያዝበት የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊዎችም ተጠይቀው ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት ተለይተው የሚመዘገቡበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

121. ለቱሪስቶች የተሰጡ አገልግሎቶች በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር መረጃ ሊይዙ ይገባል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም ለሚመለከተው የክልል ቱሪዝም

መሥሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቅሮ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎች በክልልና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የሚለዋወጡበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ቴክኖሎጂ ሊደገፍ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን መረጃዎች በተጠናቀረ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል እና እንስሳት ምርምር ሥርዓት አፈጻጸም

123. በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በ6ቱ (ቁሉምሳ፣ ወረር፣ ሆለታ፣ አምቦ፣ ባኮና አሶሳ) ከአካባቢያቸው ስነ ምህዳር ጋር የሚጣጣሙ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ሊውሉ የሚችሉ እና የግብርና የወጪ ምርትን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ የግብርና ምርቶች በምርምር ማዕከላቱ በእቅድ ተይዘውና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚፈለገው ደረጃ የማይከናወኑ መሆኑ፣

124. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣ደብረዘይት፣መልካሳ፣ቁሉምሳ፣አምቦ፣ባኮ፣ወረርእናአሶሳ) በፌዴራል ግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት የሌለ መሆኑ፣

125. በሁሉም ማዕከላት በሰብልና በእንሰሳት ዘርፎች በሚካሄዱ ምርምሮች አንዱ ምርምር ለሌላው የምርምር አይነት ግብአት እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎች የማይሰሩና በቡድን ሊከናወኑ የሚችሉ የምርምር ስራዎችን በቡድን የማይሰሩ በመሆኑ አንድ ሰራተኛ ሥራ በሚለቅበት ወቅት ሌላው ሰራተኛ የተጀመሩ ተግባራትን ማስቀጠል ያልተቻለ መሆኑ፣

126. የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና ሥርዓት እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ምርምር መካሄድ እንዳለበት ሃገራዊ የግብርና ምርምር ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚገልጽ ቢሆንም ያልተተገበረ መሆኑ፣

127. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ ማዕከል (Implementing Center) ሆነው የተመረጡበትን መስፈርት የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አለመቻሉን እና የልቀት ማዕከላቱ ስነ ምህዳርን፣ የህብረተሰቡን አመራረት ሁኔታ፣ የማዕከላቱን ማስፈጸም አቅም ወ.ዘ.ተ መሰረት አድርገው ያልተመረጡ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ የምድ ርባቡር ኮርፖሬሽን የባቡር መሰረተ-ልማት ግንባታ አፈፃፀም

128. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ (Guidelines for the Preparation of Public Sector Projects) አንቀፅ 3.1 ላይ መጀመሪያ የፕሮጀክት ምልመላ ይደረጋል፤ ፕሮፋይል በተዘጋጀላቸው ፕሮጀክት ሃሳቦች ላይ ዝርዝር ጥናት ከመደረጉ አስቀድሞ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ይዘጋጅና ቅድሚያ የሚሠጣቸው የፕሮጀክት ሃሳቦች ወደ ዝግጅት ሂደት እንዲገቡ ይደረጋል ቢልም በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ያሉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎቹ በ1999 ዓ.ም በትራንስፖርት ሚኒስቴር መሪነት አጥኚ ግብረ-ኃይል (Technical Advisory Group) ተቋቁሞ አማራጭ የየብስ ትራንስፖርትን አስመልክቶ ያደረገው ጥናት እንጂ እያንዳንዱን ፕሮጀክት አስመልክቶ የተጠና የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ (Project proposal) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤

129. የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶቹ ክትትል፣ ቁጥጥሩና ድህረ ትግበራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፕሮጀጀክት አዘገጃጀት ማኑዋል መሰረት ሊካሄድ እንዲሁም ለክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ሰነዶች መሟላት ያለባቸው ቢሆንም ለአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ግንባታ የሚያገለግል በኮንትራት ውሉ ውስጥ የተጠቀሱ ለግንባታ ስራ፣ ለቁጥጥርና ክትትል አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችና ማኑዋሎች ለምሳሌ Quality assurance manual, Lab-equipment manual,

Original design document, etc (English versions) ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ባለመሟላታቸው ውሉ ውስጥ በተጠቀሰው የጥራት መስፈርት መሠረት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ለመከታተል አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረጉ ታውቋል፡፡

130. ማንኛውም ፕሮጀክት ከመተግበሩ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊደረግና በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሊያገኝ የሚገባ ቢሆንም በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ካሉት ውስጥ የድሬደዋ አዲጋላ እና የአዳማ ሜኤሶ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቱ የተደረገው ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ መሆኑ፤

131. በፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ የሚጠቀሱ ስራዎች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ባሉ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ የተጠቀሱ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ እንዳልሆነ ለምሳሌ በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በርካታ የቱሪስት መተላለፊያ መንገዶችን ሳያስፈቀዱ መዝጋት፣ የፓርኩን ንፅህና አለመጠበቅ፣ ያለፈቃድ መንገዶችን በፓርኩ ውስጥ እየቀደዱ ማውጣት፣ በፕሮጀክቶቹ የሚሠሩ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች የዱር እንስሳትን ያለፈቃድ እያደኑ ለምግብነት የሚጠቀሙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

132. በሜኢሶ ደዋሌ የባቡር መስመር ግንባታ ያለውን የእሳተ ገሞራ የመከሰት ሁናቴ ሊገመግም የሚችል ጥናት በኮርፖሬሽኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የቻይና ተቋራጭ ከሆነው CCECC ጋር በ2011 እ.ኤ.አ በተዋዋለው የውል ሰነድ ተቋራጩ ባቀረበው Technical Proposal ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ያለው የእሳተ ገሞራ 0.5 cm per year rift እንደሚያደርግ ተጠቅሶ ይሄ ትልቁ ሪፍት ቫሊ አሁንም ሪፍት እያደረገ እንደሆነና በዚህም ምክንያት አሁንም በላይኛው የምድር አካባቢ ያለው ክፍል ላይ ከፍተኛ (The great rift valley is still rifiting currently, which results in active crustal movement & frequently occurrence of volcanic eruption & earthquakes) እንቅስቃሴዎች እንዳሉ፣ በተደጋጋሚ ጊዜ ፍንዳታዎችና የመሬት መሰንጠቆች እየተከሰቱ እንደሆነና ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ በዝርዝር የተጠናና የሚታወቅ Sesmic data እንደሌለ ስለዚህ የእሳተ ገሞራ

የመከሰት ሁናቴውን አስተማማኝ ለማድረግ የእሳተ ገሞራ የመከሰት ሁናቴ ሊገመግም የሚችል ጥናት መደረግ እንዳለበትና ኮርፖሬሽኑ ከአገር ውስጥ ብቃት ባለው ድርጅት አስጠንቶ ጥናቱን እንዲሰጣቸው ቢገልጹም ጥናቱ እንዳልተከናወነ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

133. የባቡር ፕሮጀክቶቹ ሲተገበሩ ከኮንትራት ውሉ ውጪ ለሚጨመሩና ለሚቀነሱ ጉዳዮች ኮርፖሬሽኑ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ እንዲፈቀዱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም የሰበታ ሜኤሦ ፕሮጀክት ከ1,639,031,409 የአሜሪካ ዶላር ወደ 1,841,407,000 የአሜሪካ ዶላር ኮንትራት ዋጋው ማለትም ወደ 202,375,591 ዶላር ቢጨምርም ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

134. ኮርፖሬሽኑ ሃገራዊ የባቡር ምህንድስና (Railway engineering) እና የዲዛይን ኮዶች (Design Codes) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ የተለያዩ የውጪ አገር የባቡር ስታንዳርዶችን የተከተሉ የዲዛይንና ግንባታ ስምምነቶች የፈረመ መሆኑ፣ የEPC Turnkey Contract ከተፈራረማቸው የተለያዩ አገር ተቋራጭ ኩባንያዎች የራሳቸውን ስታንዳርድ እንዲጠቀሙ መስማማቱ እና በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ያሉት ሁሉም የባቡር ግንባታዎች ማለትም የአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት፣ የአ.አ-ሰበታ-ሜኤሶ ፕሮጀክትና ሜኤሦ-ደወሌ ፕሮጀክቶች የባቡር ግንባታዎች በቻይና Railway Engineering Standard Class II እየተሰሩ መሆናቸው፣ ተቋራጮቹ የስታንዳርዱን እንግሊዝኛ ኦሪጂናል ሰነድ (Chinese Design Standard English Version) እስካሁን ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆናቸውና በዚህም በርካታ ችግሮች እየተፈጠሩ እንዳሉ፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያማከለ ሃገራዊ የባቡር ምህንድስና (railway engineering) እና የዲዛይን ኮዶች (Design Codes) ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ሊፈጅበት መቻሉና የራሺያ አገር ዩንቨርሲቲ ከሆነው ሴይንት ፒተስበርግ የባቡር ዩንቨርሲቲ ጋር በመሆን በMay 2014 የሲቪል ሥራውን ማለትም Geometric Design of Railway፣ Track Superstructure፣ Railway Subgrade፣ Bridge and Culverts እና Tunneling ቢጨርስም አሁንም ሙሉ ለሙሉ የስታንዳርዱ አዘገጃጀት አካል የሆነው የኤሌክትሮሚካኒል ሥራው አለመጠናቀቁ ታውቋል፡፡

135. የሰበታ-ሚኤሶ የባቡር መስመር አቋርጦት በሚያልፈው አዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የእንስሳት ዝውውር እንዳይስተጓጎል እና ተሽከርካሪዎች እንዲተላለፉ ኮርፖሬሽኑ ከኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በ12/10/2003 ዓ.ም 11 የእንስሳትና 2 የተሽከርካሪ መተላለፊዎች እንዲሰሩ ስምምነት ቢያደርግም አለመሰራታቸው፤

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ

136. የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ያልዘረጋና የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ የንብረቶቹን ሙሉ መረጃ ማለትም መቼ እንደ ተወረሱ፣ መቼ እንደ ተወገዱና ያልተወገዱ ንብረቶችን የሚገልጽ የመረጃ ቋት/ data base/ የሌለው መሆኑ፤

137. በባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡና በማውደም የሚወገዱ የተወረሱ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በተሟላ እና በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

138. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የእቃዎችን ዋጋ ለመተመን የሚጠቀምበት የዋጋ መተመኛ ሲዲ በየጊዜው ወቅታዊ መሆን ያለበት ቢሆንም ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አንድ አይነት መስፈርት ላላቸው ዕቃዎች የተለያየ ዋጋ የሚተመን መሆኑ እና የሲዲ ዋጋ አተማመኑ የንብረቶቹን ሁኔታ ያላገናዘበ የተጋነነ ዋጋ የሚተመንበት አሰራር በመኖሩ ምክንያት እቃዎቹ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜያት የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ፤

139. ባለስልጣኑ በጉምሩክ እና በታክስ ዕዳ ለተወረሱ የተለያዩ ንብረቶች እስከሚወገዱ ድረስ እንደ እቃዎቹ ዓይነትና ባህሪይ ተለይተው መቆየት የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያላዘጋጀ ከመሆኑም በላይ ንብረቶች በመጋዘን

ውስጥ በሚቀመጡበት ጊዜ ይዞታቸውንና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለቁ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ አለማድረጉ፤

140. በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በባለስልጣኑ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 56/2003 መሰረት በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጋቸውን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም በተለያዩ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሲወጡና ወደ ሀገር ሲገቡ የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በ48 ሰዓት ውስጥ ከተያዙበት ቅ/ጽ/ቤት በወቅቱ ገቢ ስለ መደረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሰ ስድስት ሺህ (6000) የአሜሪካን ዶላር እና 3000 የሳውዲ ሪያል ከአራት ወር በላይ ገቢ ሳይደረግ በመቅረጫ ጣቢያው የሚገኝ ሲሆን ለባለስልጣኑ መ/ቤቱ በወቅቱ ገቢ አልተደረገም፡፡

141. በቅ/ጽ/ቤቶች የተያዙ የከበሩ ማዕድናት በተያዙ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ሊደረጉና ወደ ገቢ ሊቀየሩ የሚገባ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ቅ/ጽ/ቤቶች አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምንነታቸው ያልታወቀ 55 ኪ.ግ የተወረሱ የከበሩ ማዕድናት ከአምስት ዓመት በላይ የተቀመጡ ሲሆን እንዲሁም መጠናቸው ያልታወቀ ማዕድናት በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ ቢሆንም ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ እና ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አልተደረጉም፡፡

142. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ከሚያስወግድበት መንገድ አንዱ በዱቤ ሽያጭ ሲሆን በዚሁ መሰረት ለጅንአድ በዱቤ ሽያጭ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉ ዕቃዎች እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም በውሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ አንቀጽ 3.4 መሰረት በ120 ቀን ውስጥ መከፈል የነበረበት ብር 343,205,205.36 እና ከአዲስ ፋና ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም ብር 311,293.30 ያልተሰበሰበ ሲሆን እንዲሁም በወሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ አንቀጽ 3.5 መሰረት በወቅቱ ገቢ ካልተደረገ በሀገሪቱ ከፍተኛ የወለድ መጠን መሰረት ይከፈላል የሚል ቢሆንም ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ፈቃድ አስተዳደር፣ ግብይትና ቁጥጥር

143. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይትን ለማስፋፋት፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅን መሰረት አድርጎ የማስፈፀሚያ ደንብ እንዲወጣላቸው ሊያዘጋጅ፣ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና የቀድሞውም ስራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 እና 678/2002 የማስፈፀሚያ ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲፀድቅ አላደረገም፡፡ በአሁን ወቅት በስራ ላይ ያለው የማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 182/1986 ከአዋጅ ቁጥር 678/2002 በፊት የወጣና በተጠቀሰው አዋጅ የተደነገጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የማያካትት በግልፅና በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማብራሪያዎች ባለመኖራቸው በአፈፃፀም ላይ ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይት አስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን መሰረት አድርጎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመርያ አለማዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

144. በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ሚ/ር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት መቋቋም እንዳለበት ቢደነገግም ይህ ኦዲት እስከሚጠናቀቅ በአዋጁ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡ እንደዚሁም ከሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ ካገኙ ከአምስት የከበሩ ማዕድናት አምራች ባለፈቃዶች ውስጥ ሚ/ር መ/ቤቱ ለ3ቱ (60%) ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይሁንታ ማግኘታቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

145. ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ሰዎች/ ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት፣ የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውንና የከበረውን ማዕድናት ፕሮሰስ ያደረገውን አካል ስምና የፈቃድ ቁጥሩን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ ስርዓት በመዘርጋት እንደማይከታተል ታውቋል፡፡

146. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 20 ዓመት፣ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 10 ዓመት እና የባህላዊ ማዕድን የማምረት የፈቃድ ጊዜ 3 ዓመት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች ከፈቃድ ዘመናቸው በላይ ፈቃዱን ይዞ የመቆየት እና ወደ ሌላ የፈቃድ ደረጃ ያለመሸጋገር ችግር መኖሩን ከነዚህም ውስጥ በደቡብ ፈቃድ ከወሰዱት 16 ባለፈቃዶች ውስጥ 15ቱ፣ በኦሮሚያ ከ65 ባለፈቃዶች ውስጥ 56ቱና በትግራይ ክልል 78 ባለፈቃዶች በአዋጁ መሠረት በባህላዊ የማምረት የፈቃድ ዘመናቸውን ጨርሰው ፈቃድ ያልመለሱ እንዲሁም የፈቃድ ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደሌላ የፈቃድ ደረጃ ሳይሸጋገሩ ከ9 ወራት እስከ 11 ዓመታት በማስቆጠር በፈቃዱ እንደተጠቀሙ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

147. ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ ለከበሩ ማዕድናት 8%፣ በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6% ሮያሊቲ፣ ተመን ላልወጣለት ማዕድን ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያ ተመን በማውጣትና ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በወጣው ህግ መሰረት እንዲሁም የመሬት ኪራይና ሌሎች (የመንግስት ነፃ ድርሻና ግብር) ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ተከታትለው የማይሰበስቡና የማይመረምሩ በመሆኑ በ2005 ዓ.ም ኦሮሚያ ክልል ከብር 426,982,815.56 በላይ ከሮያሊቲ ገቢ ያጣ መሆኑ፤ እንዲሁም ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት የሮያልቲ አከፋፈልን በተመለከተ የቀድሞ አዋጅ ላይ ለከበሩ 5% እና በከፊል ለከበሩ ያልተገለፀ ሲሆን፤ በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ደግሞ 8%ና 6% ቢልም ከሜድሮክ ጎልድ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት ላይ ሮያሊቲ በ5% ብቻ በመሰብሰቡ ከ2004-2006 በጀት ዓመት ከወርቅ በ3% ማለትም ብር 252,961,236.45 የሮያሊቲ ገቢ ሳይሰበሰብ መቅረቱ፤

148. በሚ/ር መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩት በደቡብ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ውስጥ በሶስቱም ክልሎች ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው የማዕድን ባለፈቃዶች በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ፈቃዳቸውን እንደማያሳድሱ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ2004-2006 በጀት ዓመት በትግራይ 119 ባለፈቃዶች፣ በኦሮሚያ 53 ባለፈቃዶች እንዲሁም በደቡብ ክልል 8 የአዘዋዋሪ

ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ሳያሳድሱ ግብይት በማከናወንና ለባንኮችም ወርቅ በማቅረብ ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ምርትና ምርመራ ላይ ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ፈቃድ ካገኙት ውስጥ 90ዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠጣቸውን የቆይታ ጊዜ ጨርሰው በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ ከ1 እስከ 15 ዓመታት ፈቃዱን ይዞ በመቆየት በመሥራት ላይ መሆናቸው እንዲሁም 14ቱ ደግሞ በአዋጅ 678/2002 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀስ 1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት የመጀመሪያ የፈቃድ እድሳት ከ1 እስከ 5 ዓመት በመዘግየት ያሣደሱ መሆኑ እንዲሁም ሌሎች ሶስት ባለፈቃዶች ደግሞ የፈቃድ ዘመናቸው ከተቃጠለ ከ3-6 ዓመታት ያስቆጠሩ ቢሆንም ፈቃዱ ያልተሰረዘ ወይም ያልታገደ መሆኑ፤

150. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ… ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ አያያዝ ዘዴ ካዳስተር ሲስተም እንዳለው ቢገልጽም ከክልሎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ የተደራረቡ የፈቃድ ቦታዎች እንደሚሰጡ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም

151. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኢትዮጲያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ያላትን አቅምና ተወዳዳሪነት (Comparative advantage) ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በክፍለ አህጉር ደረጃ በተለይም በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ ውጤታማ የሆኑ አገሮችን ተሞክሮ በመቀመር በዘርፉ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሀብቶችን በተሻለ ለመሳብ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘበ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂነት ያለው እና አስተማማኝ የድጋፍ ማዕቀፍ (Comprehensive incentive package) ያልተዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ ባለሀብቶችም እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑ፣

152. በሁሉም ክልሎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆን መሬቶች የተለዩ ቢሆንም ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ያሉት የተለዩ መሬቶች በትክክል ለዘርፉ የሚውሉ

ስለመሆናቸው በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ጥናት ያልተከናወነባቸው እና መሰረታዊ መረጃዎች ተለይተው ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፣

153. ከ2003-2006 ዓ.ም በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለተሰማሩ 38 ባለሀብቶች ከተላለፈ 16,756 ሄክታር መሬት ውስጥ እስከ 2006 የለማው 11,517 ሄክታር (69%) ብቻ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 11 ባለሀብቶች ወደ ልማት ያልገቡ ሲሆን፤ ወደ ልማት ከገቡት 27 ባለሀብቶች ውስጥ ደግሞ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆኑ፣ ከፊሎቹ የኤክሰፓርት አትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ለማምረት እና ኤክስፖርት ለማድረግ ውል ቢገቡም ለሀገር ውሰጥ ገበያ የሚያቀርቡ፣ የኤክስፓርት ስራቸውን ያቋረጡ እና ከውል ውጪ የሚያመርቱ ባለሀብቶች መኖራቸው፣ በአጠቃላይ ኤጀንሲው ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች እና የተሰጡ ድጋፎች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የክትትል ሂደቱ የተጠናከረ አለመሆኑ፣

154. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከክልሎች ጋር በመተባበር የኤክስፖርት ምርት ማምረት የሚችሉ የኮንትራት አርሶ አደሮችን (አውትግሮዎሮችን) ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ምቹ በሆኑ ክልሎች እንዲደራጁና ወደ ምርት እንዲገቡ እና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎችና የቴክኒክ ድጋፎችን በመቂ አካባቢ ላሉ አውትግሮዎሮች የሚያደርግ ቢሆንም በሌሎቹ አካባቢዎች ያልተስፋፋ መሆኑ፣ እንዲሁም የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውትግሮዎሮች) ማበረታታት የሚችሉ የግብይት፣ የብድርና የሎጀሰቲክስ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሟላላቸው የድጋፍና ክትትል ስርዓቱ ያልተጠናከረ መሆኑ፣

155. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጉዋቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ ያለመሰራታቸው፣ በተጨማሪም ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ የገበያውን መስፍርት/ስታንዳርዶች/ የማያሟሉ መሆኑ፣

156. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በመሬት አሰጣጥ፣ በመሰረተ ልማት ማሟላት፣ በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ በአጠቃላይ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ ያለመሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት በእቅድ የማይመራ መሆኑና ከኦሮሚያ ክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ቢሆንም መደበኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ እየተካሄደ ያለመሆኑ፣

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አሰባሰብና አስተዳደር

157. ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈን የግል ድርጅት አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሰራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደሞዛቸው ቀንሰውና የድርጅቱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ እንዲከፍል ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም የግል ድርጅቶቹ በአዋጁ መሠረት በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል የተዘረጋ ጠንካራ ሥርዓት የሌለ በመሆኑ በናሙና በታዩት በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ሪጅን፣ በደብረማርቆስ፣ በጎንደር፣ በሆሳዕና፣ በአዲስ አበባ በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም በዋናው መ/ቤት ከ3 ወር እስከ ሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በላይ የማይከፍሉ ድርጅቶች ከመኖራቸውም በላይ በዋናው መ/ቤት ብቻ ከሐምሌ 2003 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ከተለዩት 557 ድርጅቶች ውስጥ 500 የሚሆኑት ከ5 ወር በላይ ያልከፈሉና ከነዚህ ውስጥ 342ቱ ከዓመት በላይ ያልከፈሉ ድርጅቶች መኖራቸው፣ እንደዚሁም በጎንደር ወደ 1000 የሚጠጉ የእርሻ ባለሀብቶች የራሳቸውን ድርሻና የሠራተኞቻቸውን ጡረታ መዋጮ ሰብስበው ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፣

158. ኤጀንሲው ከገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ትልፍልፍን በተመለከተ በ29/08/05 ባስተላለፈው መመሪያ በወሩ መጀመሪያ እስከ 15ኛው ቀን የተሰበሰበውን በ16ኛው ቀን እና ከ16-30ኛው ቀን የተሰበሰበው በሚቀጥለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንድ መቶ ብር ብቻ በባንኩ ቀሪ ሆኖ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወዳለው የኤጀንሲው የባንክ ሂሣብ ቁጥር እንዲተላለፍ ለባንኮች መመሪያ ቢወርድም እየተተገበረ አለመሆኑና ወደ ብሔራዊ ባንክ ተላልፈው ነገር ግን

ብሔራዊ ባንክ ሳይገቡ እስከ 8 ወር የሚቆይ ገንዘብ መኖሩ እንዲሁም ከገቢዎችና ጉምሩክም ሆነ ከንግድ ባንክ እስከ 1 ዓመት ሳይተላለፉ የቆዩ ገንዘቦች መኖራቸው፣

159. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአት ሊዘረጋ የሚገባ ቢሆንም በናሙና በታዩት በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ሪጅን፣ በአዲስ አበባ በሰሜን፣ በምዕራብና በደቡብ ሪጅን ያልከፈሉ ድርጅቶች መረጃዎች ተለይተው አለመያዛቸው፣ በዋናው መ/ቤት መረጃው ቢኖርም ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ምን ያህል እንዳለባቸውና ከመቼ እስከመቼ መሆኑን ጥሪት ባለ መልኩ የማያሳይ መሆኑ፣

160. በመሆኑም ሁሉም የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ፣ በቀጣይም ለሚያካሄዱ ሥራዎች እንደ ግብአት በመውሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንደይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

161. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች፣ በሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 6 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ በዚህም ምክንያት በመደበኛው የኦዲት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮብን አልፏል፡፡.

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

162. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 92 መ/ቤቶች እና 18 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፤ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ መርሀ-ግብሩን የላኩት 35 የፋይናንሻልና ህጋዊነት እና 12 የክዋኔ (ዝርዝሩን በአባሪ 2 ላይ ይመልከቱ) ኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡

163. በሌላ በኩል የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ32 መ/ቤቶች እና 7 ቅ/ጽ/ቤቶችና ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ መ/ቤቶች መኖራቸው የ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ሲከናወን በተፈፀመ የክትትል ኦዲት ተረጋግጧል፡፡

164. በአንፃራዊ መልኩ በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ የመውሰዱ ዝንባሌ ከ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በኋላ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ እያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

ለኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ መስጠትና መከታተልን በተመለከተ

165. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 16 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከጥር 2005 እስከ ታህሣሥ 2006 ባለው ጊዜ ለ17 የግል ኦዲተሮችና 147 ሂሣብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡

166. በሌላ በኩል ቀደም ሲል ፈቃድ በተሰጣቸው ላይም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የ528 የሂሳብ አዋቂዎችና የ108 ኦዲተሮች ዓመታዊ የሙያ የሰርትፍኬት ዕድሳት የተከናውነ ከመሆኑም በላይ የስም ዝርዝራቸውም በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ ከዚህ ውጪ አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉት ሲያጋጥሙ

ሕገ ወጥ በመሆናቸው ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲያመች ኅብረተሰቡ ለመ/ቤታችን ጥቆማ የሚቀርብበትን ሥርዓት እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡ ከጥር 2007 ጀምሮ ይህ ሥልጣን በህግ ለሌላ አካል በመሰጠቱ በመ/ቤታችን በኩል ይከናወኑ የነበሩ ተግባራት ቀሪ ሆነዋል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

167. በዚህ ረገድ ሥራዎቹን ተቋሚዊ ለማድረግ ታስቦ ሥራዎቹን በቋሚነት የሚመራ ክፍል የተደራጀ ቢሆንም፣ በውስጥ ዕድገትም ሆነ በቅጥር የሥራ መደቦቹን ማሟላት ባለመቻሉ በሥርዓታ ፆታ፤ በHIV/AIDS እና በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከመ/ቤቱ አስፈላጊው ድጋፍ እየተሰጠ ሥራዎቹን በሚያስተባብሩ ፈቃደኛ ኮሚቴዎች አማካይነት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንና የHIV/AIDS ቀን በመ/ቤት ደረጃ ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤታችን ሴት ሰራተኞች በየሁለት ወሩ ግማሽ ቀን ቋሚ የጋራ የምክክርና የልምድ መለዋወጫ መድረክ እንዲኖራቸው ተወስኖ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዓል አከባበርን ምክንያት በማድረግ በኮሚቴው አስተባባሪነት የመ/ቤቱ ሰራተኞች የአምሊን ፊስቱላ ሆስፒታልን በመጎብኘት የፊስቱላ ተጎጅዎችን በማጽናናት በፈቃደኝነት ደም ልገሳ አድርጓል። ነገር ግን እንደተጠቀሰው ስራዎቹን በቋሚነት መደበኛ ሠራተኛ ተመድቦላቸው እንዲከናወኑ ለማድረግ በርካታ ጥረት ቢደረግም ባለመሳካቱ አሁንም መ/ቤቱ የተለያዩ አማራጮችን በመመልከት ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

168. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 419 እና ለድጋፍ ሰጪ 264 በድምሩ 683 ሲሆን፣ በጥር ወር 2006 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 244 ኦዲተሮችና 160 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 404 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 58 ኦዲተሮችና 31 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ 1 ሰራተኛ በዝውውር በድምሩ 90 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 9 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 5 በሞት የተለዩ 1 በዲሲፒሊን ቅጣት፣ 53 ኦዲተሮችና 23 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 91 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

169. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 173 ወንዶችና 88 ሴቶች በድምሩ 261፣ የድጋፍ ሰጪ 62 ወንዶችና 74 ሴቶች በድምሩ 136 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአጠቃላይ 397 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 286 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

የ2006 በጀት ዓመትና 2007 በጀት ዓመት

የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

170. በ2006 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 21,970,768.37 በጀት ተፈቅዶ ብር 21,020,087.19 ወይም 95.67% ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ ለ2007 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ብር 23,259,830.00 ተፈቅዷል፡፡ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2007 ሥራ ላይ ለማዋል የታቀደው ብር 17,447,272.20 ሲሆን የዘጠኝ ወር የበጀት አፈፃፀም ደግሞ ብር 17,318,858.10 ወይም 99.26% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

171. መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፣ በተለይ ከሰው ሀይል ፍሰት ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች ምክንያት ያሰበውን ያህል ውጤት ማስገኘት አልቻለም፡፡ በሥራ ላይ እየተፈታተኑን ከሚገኙ ተግዳሮቶች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

172. እንደለፉት ዓመታት ሁሉ አሁንም ቀልፍ የመ/ቤቱ ችግር ሆኖ የቀጠለው ኦዲቱን በሚፈለገው ጥልቀትና ጥራት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዘ ለማቆየትም ሆነ ለመቅጠር አለመቻሉ ነው፡፡ ም/ቤቱና የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ባደረጉት ጥረትና ድጋፍ ከሀምሌ 2006 ጀምሮ የመ/ቤቱ የደመወዝ ስኬል በምርጫ ቦርድ የደመወዝ ስኬል መሠረት እንዲሆን ተፈቅዶ ቢተገበርም ከሀምሌ 2006 ጀምሮ ለሌሎች የሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ መ/ቤታችን እንዳያካትት በመደረጉ የተፈቀደው የደመወዝ ስኬል ያስገኝ የነበረው ፋይዳ እንዲቀለበስ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ፈጣን ዕድገት የሂሳብና ኦዲት ባለሙያዎች ፍላጎት በከፍተኛ መጠን በማደጉና በሌላ በኩል ደግሞ

የእነኚህ ባለሙያዎች አቅርቦት ከፍላጎት ጋር ባለመጣጣሙ ችግሩን አባብሶታል፡፡ በተለይ የቁልፍ የሰው ሀይል ፍሰቱ ችግር በተለየ ሁኔታ ታይቶ ሊፈታና በፍጥነት መፍትሄ ሊያገኝ ይገባል፡፡

173. ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር በአብዛኛው መሻሻል ያሳየ ቢሆንም አሁንም በተወሰኑ መ/ቤቶች ያለመተባበር (በወቅቱ የሥራ ቦታ ያለማመቻቸት፣ መረጃ ያለመስጠት፣ የመውጫ ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠየቁ አለማመቻቸት፣ መውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ማስረጃ ለማቅረብ መሯሯጥ) ችግሮች የሚታዩ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

174. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ እስከ መስከረም 30 ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ ቢኖርባቸውም 71 መ/ቤቶች ወይም 52.98% (ዝርዘሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ) የሚሆኑት ሂሳባችውን ከጥቅምት1/2007 እስከ መጋቢት 16/2007 ድረስ በማዘግየት የዘጉ በመሆኑ የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በታሰበው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻል፣ በኦዲተሮቻችንና የስራ ኃላፊዎች ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና ከመፍጠሩም በላይ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመርሀ-ግብራችን መሠረት እንዳንጀምርና ዓመታዊ ሪፖርታችንንም በወቅቱ እንዳናዘጋጅ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖብን አልፏል፡፡

175. መ/ቤቶች ሂሳባቸውን ህጉ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ዘግተው ለኦዲት የማያቀርቡ ከሆነ ኦዲቱን አቋርጠን ለመውጣት ወስነን ሠርኩለር ያስተላለፍን ቢሆንም ጉዳዩን በማስታመም ኦዲቱን ከማቋረጥ ይልቅ የየመ/ቤቶቹን የበላይ ኃላፊዎች በተደጋጋሚ በማነጋገርና ጥረት እንዲያደርጉ በመገፋፋት ኦዲተሮቻችንና የስራ ኃላፊዎቻቸውን ከመደበኛ ሥራ ሰዓት ውጭ ያለምንም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በማሠራት የዘመኑን የኦዲት ሥራ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ሂሳብን በወቅቱ አለመዝጋትና በህግ በተቀመጠው አግባብ ለኦዲት ኣለማቅረብ የሕግ ጥሰት በመሆኑ ለወደፊቱ እንዳይደገም መ/ቤቶች ከወዲሁ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ሂሳባቸውን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ ባስቀመጠው የሕግ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዘግተው ለኦዲት እንዲያቀርቡ ግፊት እንዲደረግና በማያቀርቡት ላይ ም/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

176. በአብዛኛው መ/ቤቶች አሁንም የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሎች በመዋቅር፣ በክህሎትና በዕውቀት በሚገባ ባለመደራጀታቸውና አንፃራዊ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ባለመደረጉ ወይም ባለመፈቀዱ የውጪ ኦዲቱ ከውስጥ ኦዲት ሥራ ማግኘት የሚገባውን ያህል ፋይዳ በዚህም ዓመት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ጥረቶች በመደረጋቸው የተወሰነ ለውጥ ቢኖርም አሁንም የታሰበውን ወጤት ባለማስገኘቱ ጥረቱ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

177. የተወሰነ መሻሻል የሚታይ ቢሆንም አሁንም በርካታ ኦዲት ተደራጊዎች ከመ/ቤታችን በሚላኩ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ መልስ ያለመስጠትና በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረትም በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰድ አሁንም ያልተፈታ ችግር ነው፡፡ በተለይም በተደጋጋሚ ሂሳባቸው ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት የማይቻልና ተቀባይነት የሚያሳጣ ኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር ህጎችና መመሪያዎችን ተከትለው የሂሳብ ሪፖርታቸውን ሊያቀርቡ ይገባል፣ ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ሊቀጥል ስለማይገባና ከፍተኛ ተጠያቂነትን ጭምር የሚያስከትል በመሆኑ አሁንም የሚመለከታቸው አስቀድመው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ይመከራል፡፡ በም/ቤቱም በኩል የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ

178. የሰው ሀይል ፍሰቱ ፈታኝ ቢሆንም ችግሩ በሚመለከተው አካል ተገቢውን መፍትሄ እንደሚያገኝ ታሳቢ በማድረግ በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብም የኦዲቱ ሽፋን 100% ሆኖ እንዲቀጥል በ146 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ ላይ የሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ የኦዲት ጥራት የሁሉም ኦዲት ፈፃሚ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጎ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ተነድፏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከየካቲት 2007 እስከ ጥር /2008 ድረስ 20 የክዋኔ ኦዲቶችን በማከናወን 19 ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩል ከጥር 2007 እስከ ታህሣሥ 2008 ድረስ በ300 የመሠረታዊ

አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

179. በዚሁ መሠረት ከመጋቢት እስከ ሚያዝያ 30/2007 ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በ41 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደግሞ ካለፈው ዓመት የዞሩ 3ቱን ጨምሮ 18 የክዋኔ ኦዲቶች እና 46 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲቶች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና

በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

180. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

181. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2006 በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

182. በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 78 ሲሆኑ፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሣብ ደግሞ 174 በድምሩ 252 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት

ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

183. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፤ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) 161፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Qualified opinion) 71፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) 18፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቃውሞ አስተያየት የቀረበባቸው (Adverse) የተሰጠበት 1 እና አስተያየት ያልተሰጠበት ልዩ ኦዲት 1 በድምሩ 252 ናቸው፡፡

184. በሌላም በኩል መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 17 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን

የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች

185. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማው፤ የመንግስት ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት ማበርከት ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን

186. በ2006 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 112 የሰው ኃይል 240 ኦዲቶችን ለማድረግ አቅዶ 235 ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱ 97.91% ለመፈጸም ችሏል፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

187. ኮርፖሬሽኑ በ2006 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 18,400,062.00 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 16,405,543.00 ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 11,063,550.00 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 10,370,895.00 ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር 5,135,559.00 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

188. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ አንድ መ/ቤት ሂሳቡን ባለመዘጋቱና ሌላ አንድ መ/ቤት በሰው ሀይል እጥረት ተጀምሮ ባለመጠናቀቁ የኦዲት ሽፋኑን 98.52% ሆኗል፡፡ የክዋኔ ኦዲቱም 20 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ከታቀደው የ18 (90%) ሲጠናቀቁ፣ ሌሎች በዳሰሳና ቅኝት ኦዲት ደረጃ የሚገኙ 3 ክዋኔ ኦዲቶች በዕቅዱ መሠረት ወደ ቀጣዩ ዓመት ተላልፏል፡፡ የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲት 300 ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡ በዋንኛነት ከሰው ሀይል ፍሰት ጋር በተያያዘ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋን ባለፈው ዓመት ከደረሰበት 100% ወደ 98.52% መውረዱና የክዋኔ ኦዲቱም በ10% ከዕቅድ በታች መፈጸሙ የደረስንበትን ደረጃ ቀጣይ ከማድረግ አንፃር በሰው ሀይል ፍሰት ምክንያት በሥራችን ላይ ምን ያህል ፈተና እየገጠመን መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ፍሰቱ አሁንም በመቀጠሉ ስለሆነም አሁን የተደረሰበት ደረጃ ወደ ኋላ እንዳይንሸራተት የም/ቤቱ ድጋፍ እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ጉዳዩ በልዩ ትኩረት ሊታይ ይገባል፡፡

189. ቀደም ሲል ከተገለጹት ሁለቱ መ/ቤቶች ውጭ ውዝፍ የኦዲት ሥራ አለመኖሩና የተቀሩትን የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በየዓመቱ ኦዲት በምናደርግበት ደረጃ ላይ መገኘታችን የአሠራር ክፍተቶችን በፍጥነት በመለየት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ጥረቱ አሁንም ሊጠናከር ይገባል፡፡ ነገር ግን በተደጋጋሚ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ሆኖም ትኩረት ተሰጥቶዋቸው ቢሆን ኖሮ ሊወገዱ የሚችሉ ግድፈቶች በዚህም ዓመት መ/ቤቶች ማረም አለመቻላቸው አሁንም የቱን ያህል ትኩረት ለዚህ ጉዳይ ልሰጥ እንደሚገባ አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ የተጠናከረ ክትትል ሊያደርጉና እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ18 ጥራዝ ተዘጋጅቶ፣ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፣ በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና በሌሎች

የሚመለከታቸው የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል በጥልቀት ተመርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

190. ነገር ግን እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ እየተንከባለሉ የመጡት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች በሁሉም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ሌሎች ጉዳዩ በሚመለከተው አካላት ልዩ ትኩረት አግኝተው ሊታረሙና ሊስተካከሉ ይገባል፡፡ በተለይ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ ተሰብሰቢ ሂሳቦች፤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከናወኑ ግንባታዎችና ግዢዎች በልዩ ሁኔታ ሊታዩ የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸውን ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

191. በሌላ በኩል ከመንግሥት ግንባታዎች ጋር በተያያዘ በተለያዩ ምክንያቶች በወቅቱና በተያዘላቸው በጀት ያለመጠናቀቅ ችግር፤ መፍትሔ ሣያገኙ ለረጅም ወራትና ዓመታት ጭምር የግንባታ ሂደታቸው የቆሙ ፕሮጀክቶችና የሚገናቡ ፕሮጀክቶች ጥራት አፋጣኝ እርምጃ የሚያሻው በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ለፈታ ይገባል፡፡

192. በተጨማሪም በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን በተመለከተ ም/ቤቱ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ከ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ተገቢ ነው የሚለውን እርምጃ በመውሰድ ችግሩን ለማቃለል ጥረቱን ይበልጥ ሊያጠናክር ይገባል፡፡

193. የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ በወቅቱ መዝጋት ያልቻሉ መ/ቤቶች ከጠቅላለው ከ52% በላይ ናቸው፡፡ ይህ መሻሻል ሲገባው እየባሰበት የመጣው የባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብን በወቅቱ ዘግቶ ለኦዲት ያለማቅረብ ጉዳይ በአንክሮ ሊታይና ተገቢው ህጋዊ እርምጃ መውሰድን የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ከእርምጃው ጎን ለጎን አብሮ መታየት ያለበት በየመ/ቤቱ ያለው የሂሳብ፤ የግዢና የንብረት ባለሙያዎች ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከአቅርቦትም ከክፍያ ሥርዓቱም ጭምር አብሮ ሊታይ ይገባል፡፡

194. በመጨረሻም ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በም/ቤቱና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በኩል በተደረጉት ጥረቶችና ድጋፎች ከሀምሌ 2006 ጀምሮ የመ/ቤቱ የደመወዝ ስኬል በምርጫ ቦርድ ስኬል መሠረት እንዲሆን ቢወሰንም በተመሳሳይ ጊዜ በተደረገው የአጠቃላይ የሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ መ/ቤታችንን እንዳያካትት በመደረጉ የተፈቀደው የደመወዝ ማስተካከያ ያስገኝ የነበረውን ሠራተኛ የማረጋጋት ፋይዳ ሳያስገኝ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ከተደረገበት ሀምሌ 2006 ጀምሮ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ብቻ ከ60 በላይ በአብዛኛው ቀልፍና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች መ/ቤቱን ለቋል፡፡ ይህ ችግሩ ምን ያህል አስከፊና ከወዲሁ መፍትሔ ካለገኘ በቀር የ2007 በጀት አመት ሂሰብ የኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን ሊጎዳ ይችላል፡፡ ስለሆነም እስከ አሁን የተገኘውን ውጤት ጭምር ወደ ኋላ ለመመለስና የወደፊቱንም አፈፃፀም ሊጎዳ በሚችል መጠን በሁሉም ደረጃ መ/ቤቱን እየተፈታተና የሚገኘውን የሠራተኛ ፍሰት ችግር ለማቃለል ም/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ በአክብሮት እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡